# የመልመጃ ጥያቄ መልስ

1. የሚከተሉትን አስሉና ውጤቱን በኪ.ግ አስቀምጡ።

ለ/ 6.5 ቶን + 8 ኩንታል

1ቶን = 10 ኩንታል

= 6.5 × 10 ኩንታል + 8 ኩንታል

= 65 ኩንታል + 8ኩንታል = **73 ኩንታል**

1 ኩንታል = 100 ኪ.ግ

73 × 100 ኪ.ግ

= **7,300 ኪ.ግ**

ሐ/ 150 ኪ.ግ - 65 ክ.ግ

= **85 ኪ.ግ**

# ምእራፍ አምስት

## የጠለል ምስሎችና ጠጣር ምስሎች

# ሒሳብ 4ኛ ክፍል

ተማሪዎች የዛሬው ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ❖ አንግል እንዴት  እንደሚመሰረት ታውቃላችሁ።
- ❖ የተቋራጭ  እና የቀጤ ነክ ተቋራጭ መስመር ልዩነት ትረዳላችሁ።
- ❖ ማዕዘናዊ አንግል እንዴት እንደሚመሰረት ትገነዘበላችሁ።

# 5.1 ማዕዘናዋ አንግል

ተግባር 1

1. አንግል እንዴት ይመሰረታል ?

(የተሰጠ ሰዓት 1 ደቂቃ)

**<u>ማለቱ:-</u>**


1 ሁለት ጨረር ማስመሮች የጋራ መነሻ ነጥብ ሲኖራቸው አንግል ይመሰረታል፡፡

2. ሁለት ቀጥታ ጨረር ማስመሮች ሲቋረጡ(ሲተላለፉ) አንግል ይመሰረታል፡፡

- በጨረር ማስመሮች የሚመሰረተው የጂኦሜትሪ ምስል <u>አንግል ተብሎ</u> ይጠራል፡፡

# ሒሳብ 4ኛ ክፍል


- የጋራ መነሻ ነጥብ ባላቸው ጨረር ማስመሮች የተመሰረተ አንግልን ተመልከቱ፡፡




አንግሉን የሚፈጥሩ ሁለት ጨረሮች የአንግሉ ጎኖች ይባላሉ፡፡

# ሒሳብ 4ኛ ክፍል

- ሁለት ቀጥታ ጨረር ማስመሮች ሲቋረጡ(ሲተላለፉ) የተማሰረቱ አንግሎችን ተሜልከቱ፡፡




**<u>የተመሰረቱ አንግሎች</u>**

< ሀቀሠ


< መቀለ

< ሀቀመ

< ሠቀለ

## ቀጤ ነክ ተቋራጭ ማስመሮች፡-


- ሁለት ቀጥታ ማስመሮች ‘ሀ’ እና ‘ለ’ ቀጤ ነክ ተቋራጭ ማስመሮች ናቸው የሚባሉት ሲተላለፉ ማእዘናዊ አንግል የሚመሰርቱ ከሆነ ነው፡፡





- አራት እኩል መጠን ያላቸው አንግሎች ከተመሰረቱ እያንዳንዱ አንግል ማእዘናዊ አንግል ይባላል፡፡

**ተግበባር** 1፡ ከሚከተሉት ጥንድ ተቋራጭ መስመሮች ማዕዘናዊ አንግል የሰሩት የትኞቹ ናቸው?


የተሰጠ ሰዓት 5 ደቂቃ




**ምስል 1፧**





**ምስል 2፡**





**ምስል 3፡**


**መልስ**፡-




- ማስመሮቹ ቋሚ ስላልሆኑ ማእዘ-ናዊ አንግል አልመሰረቱም፡፡




ማስመር ‘ሀ’ ለማስመር ‘ለ’ ቀጤ ነክ(ቋሚ) ማስመር ስለሆነ ማስመሮቹ ማእዘናዊ አንግል ማስርተዋል፡፡




- ማስመሮቹ ቋሚ ስላልሆኑ ማእዘ-ናዊ አንግል አልመሰረቱም፡፡

# ሒሳብ 4ኛ ክፍል

- በአጠቃላይ በእለቱ ትምህርት  ስለ አንግል ምንነት፣ መነሻ

ነጥብ ባላቸው ሁለት ጨረርና ተቋራጭ መስመሮች አንግል እንደሚፈጠር ፣ በቀጤ ነክ ተቋራጭ መስመሮች ማእዘናዊ አንግል እንደሚመሰረት ተምራችኋል፡ ፡

- ተማሪዎች በቤታችሁ የሚገኙ ቁሳቁሶችን በመመልከት ማእዘናዊ አንግል ቅርፅ ያላቸውን ስማቸውን በደብተራችሁ ላይ ፃፉ፡፡

- በቀጣይ ክፍለ ትምህርት በመፅሐፋችሁ ገፅ 76 ላይ ነጥቦች ፣ቀጥታ መስመሮችና ጠለሎች በሚል ርእስ ላይ ዕንገናኝ የእለቱን ትምህርት በዚህ ላይ አጠናቀናል፡፡

# ደህና ሁኑ ተማሪዎች !